ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
ሰሜን አሜሪካ ጽ/ቤት
Kinijit for Unity and Democracy Party (Kinijit)
North America Office

# በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ 2ኛ ጉባኤ የአቋም መግለጫ

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ ተወካዮች፤ ከሜይ 14 - 15፣ 2006 በዋሺንግተን ዲሲ፤ ሁለተኛ ጉባኤያቸውን አካሂደው፤ ቅንጅቱን ለማጠከር አስፈላጊ ናቸው ብለው ያመኑባቸውን የአደረጃጀት ለውጥ አድርገዋል፤ ላዕላይ ምክር ቤቱንም በኦፊሴል ሰይመዋል።

ከዚህም በተጨማሪ...
1ኛ - በወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ
2ኛ - በአገራችን የወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር የሚያደርገውን ፀረ ህዝብ አፈና ግድያና ህገ-ወጥ እብሪት በመገምገም
3ኛ - የቅንጅትን የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ እንቅስቃሴን አስመልክቶ የነበሩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ገምግሞ፤ የሚከተለውን ባለ አስር ነጥብ መግለጫ አውጥቷል።

1 - የቅንጅት መሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች፤ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች፣ የሲቪክ ማህበር አባላት ከሚገኙበት እስራት ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ የሚደረገውን ጥረት አጠናክረን ለመቀጠል ቃል ገብተናል።

2 - ከምርጫው መጭበርበር ወዲህ፣ ተፋፍሞ የቀየውን የህዝባችንን ትግል፤ ከዳር ለማድረስ በየእለቱ ስቃይ ከሚደርስበት ህዝባችን ጎን እንሰለፋለን።

3 - በኢትዮጵያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ለማድረግ ከሚጥሩ ሃይሎች ጋር ሁሉ አብረን እንሰራለን።

4 - የውጪ ዲፕሎማሲው ስራ ይበልጥ በተቀላጠፈ መልክ እንዲከናወን፤ በያለንበት የአሜሪካ ክፍለ ግዛት አስፈላጊውን የሎቢ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ወስነናል።

5 - በየአካባቢያችን ያለው ኢትዮጵያዊ በቅንጅት የአንድነትና የዲሞክራሲ ራእይ ዙሪያ ይበልጥ እንዲሰባሰብ ጥረታችን ይቀጥላል።

6 - የወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ትግል ለማኮላሸት የሚያደርገውን ሙከራ እናከሽፋለን።

7 - ቅንጅት የጀመረውን ከጥላቻ እና ከጎሰኝነት የፀዳ ፖለቲካ መሰረት በማድረግ፤ የወያኔ የዘር ፖለቲካ እንዲከስም ያላሰለሰ ሰላማዊ ትግላችንን እንቀጥላለን።

8- የቅንጅትን አቅም በሁሉም መስክ እናጠናክራለን።

9- ቅንጅት በአለም አቀፍ ደረጃ በሚያደርገው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የኢትዮጵያዊነት ግዴታችንን እንወጣለን።

10 - ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መሪዎቹ በእስር ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ መሪዎች እውቅና ወይም ይሁንታ ውጪ የሚደረግ ማንኛውንም እንቅስቃሴ አንቀበልም።

“የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት የድጋፍ ሰጪዎች ላዕላይ ምክር ቤት”
ዋሺንግተን ዲሲ፣ ሜይ 15፣ 2006።

766 Rock Creeck Church Road NW, Washington DC 20010
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: kinijitUSA@kinijit.org